# የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ማሕበር - አሜሪካ

## Kinijit Support Group – America

8605 Cameron Street, Suit M-0 Silver Spring, MD 20910

Tel (301) 565 7864, Fax 301 565 7863 e-mail kinijitusa@kinijit.org


---

# የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ማሕበራት - አሜሪካ ቻፕተሮች
# 5ኛ መደበኛ ጉባኤ
# የአቋም መግለጫና ውሳኔ

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ማሕበራት ተወካዮች 5ኛ መደበኛ ጉባኤ ፌብርዋሪ 15 እና 16 ቀን 2008 ዓ.ም በሲልቨር ሰፐሪንግ ሜሪላንድ ክራውን ፕላዛ ሆቴል በተሳካ ሁኔታ ተከሂዷል። ጉባኤው በድርጅቱ የውሰጥ ጉዳዮች ፣ በፓርቲውና በወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ የአቋም መግለጫና ውሳኔ በማሳለፍ ተፈጽሟል።

## 1. <u>የድርጅቱን የውስጥ ጉዳዮች በተመለከተ</u>

1.1 የድርጅቱ የውስጥ ጉዳዮችን በተመለከተ ባለፉት 2 አመታት ስለተከናወኑት ጉዳዮች ሊቀመንበሩ ያቀረቡትን ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ ድርጅቱ ባለፉት 2 አመታት የተጓዘበት እጅግ የተወሳሰበ የትግል ጉዞ አዳጋች የነበረ ቢሆንም ይህንን ሁሉ ተቋቁሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነትና ለዲሞክራሲ ቅንጅት እያደረገ ያለውን ጥረት በማገዝ ረገድ ያከናወናቸውን መልካም ተግባሮች አድንቋል።

በተለይም የቅንጅት አመራር አባላት በግፍ በታሰሩበት ወቅት በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የድጋፍ ድርጅቶችን ስራ በማሰተባበር ግፈኛው የወያኔ መን ግስት ያሰራቸው የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ በገንዘብ አሰተዋጽኦ ፣ በሰላማዊ ሰልፍና በዲፕሎማሲ አያሌ ኢትዮጵያውያን እንዲረባረቡ ያደረገው እንቅስቃሴ ታሪክ የሚይርሰው መሆኑን አረጋግጧል። ይሁን እንጂ የዚህ አይነቱ ታላቅ ተግባር እየተከናወነ ባለበት ወቅት ከስንዴ ውስጥ እንክርዳድ አይጠፋምና በአን ዳንድ አሳሳቾች የተነሳ የትግሉን አቅጣጫ ለማሰቀየር በተደረገ ጥረት ጥቂት አባላት በተሳሳተ መንገድ በመጓዛቸው ጉባኤው አዝኖ ወደፊት እነዚህ አባላት የሚመለሱበትንና የትግሉን ጎራ የሚቀላቀሉበት መንገድ እንዲቀየስ ጉባኤው ወስኗል።

1.2 ጉባኤው ከጃንዋሪ 2006 እስከ 2008 እ.ም ድረስ ለ 2 አመታት ሲያገለግሉ ቆይተው የአገልግሎት ዘመናቸውን የፈጸሙትን የስራ አመራር አባላት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በተመረጡ አባላት ተክቷል።

በዚህም መሰረት ለስራ አስፈጻሚ አባልነት

1. አቶ ግዛው ተስፋዬ - ሊቀመንበር
2. » ታምራት መንገሻ ተቀዳሚ ም/ሊቀመንበር
3. ወ/ሮ ዲያና ኪዳነ ማርያም 2ኛ/ም/ሊቀመንበር
4. አቶ ካሳ ገሰሰ ዋና ጸሃፊ
5. » ተስፋዬ አስፋው ዋና የገንዘብና ንብረት ሃላፊ

ለሁለት አመት እንዲያገለግሉ ሲመረጡ ለልዩ ልዩ መምሪያ ሃላፊነት ደግሞ

1. ዶ/ር አረጋኸኝ ንጋቱ
2. አቶ ኤርምያስ ከበደ
3. » ዘነበ ታምራት
4. » መለኩ ተፈራ
5. ወ/ሮ አይዳ መንግሰቱ
6. አቶ ግርማ ታፈሰ
7. » ታደለ አወቀ
8. ዶ/ር በላይ እሸቴ
9. አቶ አምሃ ውበቱ
10. አቶ ፋሲል ደምሴን መርጧል።

እንዲሁም ለኦዲት ኮሚቴ 3 አባላት ለስነ ምግባር ኮሚቴ 3 አባላት የተመረጡ ሲሆን እነርሱም፦

ለኦዲት ኮሚቴ

1. አቶ ሰለሺ ጥላሁን
2. ወ/ሮ የኔአለም ከበደ
3. አቶ ጸሃይ ደመቀ

ለሰነ ምግባር ኮሚቴ

1. ኮማንደር ጸጋዬ ውድነህ
2. አቶ ዘነበ ዓለማየሁ
3. ፐ/ር ሃብተ ጊዮርጊሰ ቸርነት ናቸው።

ጉባኤው ድርጅቱ የሚመራበትን የመተዳደረያ ደንብ መርምሮ አጽድቋል።

## 2ኛ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን በተመለከተ

2.1 ጉባኤው በቅንጅት ፓርቲ ውስጥ በተከሰተው የጥቂት አመራር አባላት ማፈን ገጥ የአዘነ መሆኑን ገልጦ ቅንጅት የተነሳበትን ግብ እንዲመታ ለመርዳት ከክቡር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል ጎን በመቆም እንደሚታገል አረጋግጧል። የቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዲፕሎማሲ ፣ በኢኮኖሚና በሕዝብ አስተዳደር ፖሊሲ እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ ጥናቶች ለፓርቲው እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ እያደነቀ በዚህ ረገድ ፓርቲውንም ሆነ የሰሜን አሜሪካ ቻፕተሮችን ለማጠናከር የሚሰጠውን ድጋፍ በሰፊው እንዲቀጥልበት ጥሪውን አቅርቧል። እንዲሁም በካውንስሉ አማካኝነት የተቁቁዋመው ታስክ ፎርስ ለቻፕተሮች ስለሰጠው አገልግሎት አመስግኗል። በተጨመሪም የቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል ሊቀመንበር ዶ/ር ታዬ ወልደ ሰማያት ለኢትዮጵያ አንድነት እያደረጉ ያሉትን ትግል ጉባኤው አድንቆ በእርሳቸው አመራር የቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል ለፓርቲው የሚያደርገው ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ከጎናቸው እንደሚቆም አረጋግጧል።

2.2 በዛሬው እለት ሃላፊነት የተረከበው አዲሱ የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጭ ማህበር አመራር አካል በአሁጉሩ ቻፕተሮች መካከል የተከሰተውን መከፋፈል በጥብቅ እያወገዘ የቻፕተሮቹን አንድነት ለመመለስ ሳይታክት እንደሚሰራ ቃል ገብቷል።

2.3 ጉባኤው ለትግላችን አጋዥ ይሆን ዘንድ ከለጋሽ ወገኖቻችን የሚገኝ ማን ኛውም እርዳታ ድጋፍ ሰጭ አካላት ዘንድ መከማቸቱ ቀርቶ ለትግሉ ስራ ማካሄጃ ይሆን ዘንድ በቀጥታ ወደ አገር ቤት የሚላክበት ሁኔታ እን ዲመቻች ወሰኗል።

## 3ኛ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታን በተመለከተ

3.1 በኢትዮጵያ ላይ ተንሰራፍቶ ያለው የወያኔ ዘረኛና የጎሳ አገዛዝ ዲሞክ ራሲያዊ ስርአትን ረግጦ ሰብአዊ መብትን በማፈን በሕዝባችን ላይ በማድረስ ያለውን ከፍተኛ በደል ጉባኤው አጥብቆ እያወገዘ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅን ጅትን ፕሮገራም መሪ በማድረግ ለመብቱና ለነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል እያደነቀ ሕዝቡ በራስ አነሳሽነት የተያያዘው መራራ ትግል ግቡን እንዲመታ ዓለም አቀፍ ዲሞክራቲክ ሃይሎች ዲፕሎማሲያዊና ቁሳዊ ድጋፍ እንዲሰጡት ጥሪውን ያቀርባል።

3.2 በኢትዮጵያ አንድነት በሚያምኑ የተቃዋሚ ኃይሎች ጎራ ውስጥ ተሰግስገው የጋራ ትግል እንዳይካሄድ በከፋፋይነትና በአንጃኝነት በተናጠል ለግል ስልጣን የሚሯሯጡ ቡድኖችን ጉባኤው በጥብቅ እያወገዘ የቅንጅት ፓርቲ አመራር አባላት ከሁሉ በፊት አንድነታቸውን በማጠናከር በትግል ከተፈተኑት መሪአች ን በክቡር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል አመራር ዙሪያ በመሰባሰብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገበውን ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለማላበስ በወያኔ የግፍ አገዛዝ ላይ እንዲረባረቡ  ጥሪውን ያቀርባል።

የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ማህበራት - አሜሪካ ቻፕተሮች 5ኛ መደበኛ ጉባኤ
ፌብሩዋሪ 16 ቀን 2008 አ.ም
ሜሪላንድ ፤ ሲልቨር ሰፕሪንግ
ዩናይትድ ሰቴትሰ ኦፍ አሜሪካ